# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 89 ጥር 20 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ወደ አረብ አገር ለግርድና ከሚላኩና በጉዲፈቻ ከሚሰጡ ዜጎች ወያኔ በርካታ ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ያገኛል

ወያኔ ወደ አረብ አገር ለግርድና በሚላኩ ኢትዮጵያዊያንና በጉዲፈቻና በማደጎ ስም ለውጭ አገር ዜጎች ከሚሰጡ ህጻናት በአመት እስከ ከአንድ ቢልዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ገቢ እንደሚያገኝ አንድ ምስጥራዊ ጥናት አጋለጠ

ከወያኔ ጋር ያላቸው የጠበቀ ግንኙነት በማይታወቅበት መልኩ ተደራጅተው በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ የንብረትና የገንዘብ ዘረፋ እየፈጸሙ ያሉትን የወያኔ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ለማጥናት የተቋቋመ አንድ ህቡዕ የባለሙያተኞች ቡድን ፤ ሰሞኑን ለግንቦት 7 በሰጠው የጥናት ማስረጃ ሥራንና ሠራተኛን በማገኛነት ሰበብ በግል ድርጅትነት ተመዘገበው የሚንቀሳቀሱት የህወአት ድርጅቶች እድሜያቸው በአስራዎቹና በህያዎቹ የሚገኙ ወጣቶችን ወደ አረብ አገራት ለግርድናና ለአሽከርነት እንዲላኩ በማድረግ እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ኮሚሽን እንደሚሰበስቡና ፣ ወደ አውሮፓና አሜሪካ በጉዲፈቻ ስም ከሚላኩ ህጻናት ደግሞ እስከ 200 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ገንዘብ በየአመቱ እንደሚያስገቡ ለማወቅ ተችሎአል።

ይህ አስደንጋጭ የጥናት ውጤት ይፋ ከተደረገ በኋላ ጉዳዩን ለህዝብ ለማሳወቅና አለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኝ ለማስቻል አንዳንድ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውንም ተያይዞ ከደረሰን ዜና ለማወቅ ተችሎአል። ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ አንድ ስማቸው እንዳይታወቅ የፈለጉት የህግ ባለሙያ ለግንቦት 7 እንደገለጹት "ወያኔ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የባሪያ ንግድ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ ፍተሻ እየተደረገ ነው፣ ምክንያቱም የጸጥታ ስጋት ነው ተብሎአል

በሰሜን ኢትዮጵያ ባለው የጸጥታ ችግር እንቅልፍ እያጣ የመጣው ወያኔ፣ በመውጪያና መግቢያ አካባቢዎች ሁሉ ከፍተና ፍተሳ እያደረገ እንደሚገን ምንጮቻችን ዘግበዋል።

በማክሰኞው ዜና በሰሜን ጎንደር የጠረፍ አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ በመምጣቱ ወያኔ ሰራዊቱን ለማስፈር እንደተገደደ መዘገቡ ይታወሳል። ሰራዊቱን፣ የአካባቢውን ታጣቂዎችና የፖሊስ አባላትን በማሰማራት የጠበቀውን ውጤት ማግኘት ያልቻለው ወያኔ፣ በአሁኑ ጊዜ ልዩ የሆነ የፈታሽ ቡድን እያቋቋመ እንደሚገን ታውቋል። ከፌደራል እስከ መጨረሻዋ ቀበሌ ድረስ የተዘረጋው የፈታሽ ቡድን፣ በብሄራዊ ደህንነት ግብረሀይል ሃላፊ በሆነው አባይ ጸሀየ የሚመራ ሲሆን፣ ከመከላከያ፣ ከፖሊስ ፣ ከጸጥታ ዘርፍ ካድሬዎችና ሲቪል ከሚለብሱ የደህንነት አባላት በተውጣጡ ሰዎች የተሞላ ነው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የኑሮ ውድነቱም ወደ ከፋ ደረጃ እያሻቀበ ነው ተባለ

በውጭ ንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለግንቦት7 ዘጋቢ እንደገለጹት በአገሪቱ ውስጥ የሚታየው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከመቼውም ጊዜ በላይ በባሰ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል። ከተወሰኑ ወራት በፊት አስመጪና ላኪዎች የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት እስከ ሶስት ወር መጠበቅ ግድ ይላቸው ነበር አሁን ግን በሰባት ወር ውስጥም ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ገልጸዋል። በዚህም የተነሳ የውጭ ንግድ እንቅስቃሴያቸውን ለመግታት እየተገደዱና ከገበያ እየወጡ ነው። ይሁን እንጅ ይላሉ ባለሀብቶቹ፣ የወያኔ የንግድ ተቋማት ከሌሎች የግል ተቋማት በተለየ ሁኔታ የውጭ ምንዛሬዎችን የሚያገኙ በመሆናቸው፣ በቀላሉ እቃዎችን አስመጥተው ወይም ወደ ውጭ ልከው የተሻለ ገቢ በማግኘት ላይ ናቸው። ለእኛ የማይቻለው ለወያኔ የንግድ ድርጅቶች ይቻላል የሚሉት አንድ ባለሀብት፣ ለእኛ የለም የሚባለው የውጭ ምንዛሬ ከየት መጥቶ ለዌአኔ የንግድ ተቋማት እንደሚሰጥ አናውቅም፤ እንደሚመስለን ግን ሰዎቹ ሙሉ በሙሉ የግለሰብ ባለሀብቶችን ከጨዋታ ውጭ በማድረግ የአገሪቱን ሃብት ሙሉ በሙሉ እነርሱ በሚመሯቸው ድርጅቶች ለመቆጣጠር አስበው የሚያደርጉት ነው። ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው የጸጥታ ሁኔታ ያሰጋው ወያኔ፣ ሰራዊቱን በአካባቢው በብዛት ማሰማራት መጀመሩን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ዜጎች ገለጹ

በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ያለውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ተመልክተው የዘገቡት ምንጮቻችን እንደገለጹት፣ በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በጎንደር አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበላሸ በመምጣቱ ወያኔ ሰራዊቱን በአካካቢው በብዛት ለማስፈር ተገዷል። ከጥር 3 ቀን 2002 ዓም ጀምሮ በሰሜን ምእራብ አቅጣጫ ማለትም ከላይ አርማጭሆ ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነው ሳንጃ ጀምሮ በሶረቃ፣ አብራጂራ እና አበድራፊ በሚባሉ በምእራባዊ ወረዳ ዋና ዋና ከተሞች ላይ እያሰፈረ ይገኛል። በሰንጃ ከተማ አካባቢ ያለው ጦር ከከተማዋ በምስራቅና በምእራብ አቅጣጫ እስከ አስሬ ከተማ ድረስ ያለውን አካባቢ የሚቆጣጠር ሲሆን፣ ጠገዴ ወረዳ ዋና ከተማ ሰሮቃ አካባቢ ያለው ደግሞ ከከተማዋ በምእራብ አቅጣጫ እርጎየ፣ ማርዘነብ፣ ኪሻንና ሚት አርጊ የሚባሉ የገጠር ከተሞችንና አካባቢውን የሚቆጣጠር ነው።

በምእራብ አርማጭሆ ወረዳ ዋና ከተማ አብራጂራ አካባቢ የገባው ጦር ዘመነመርቂን፣ ጋቭላን፣ ሲናርና ኮርሁመር የሚባሉ ትናንሽ የገጠርማ የሱዳን ጠረፍ ከተሞችንና ቀበሌዎችን የሚቆጣጠር ነው። በአብድራፊ የጠረፍ ከተማ የገባው ደግሞ አካባቢውን በማስፋት ከከተማዋ ወደ ምእራብና ሰሜን ምእራብ አቅጣጫ ወያኔ ክልሌ ነው እስከሚለው የወልቃይት መሬት ሁመራ ጫፍ ከሉግዲ ተራራ በታች አንገረብ ወንዝን አካሎ ወደ ደቡብ ምእራብ አቅጣጫ አቡጢር፣ ገላሉዋና ኮርዶም የሚባሉ የምእራብ አርማጭሆ ጠረፋማ አካባቢዎችን የሚያስስና የሚቆጣጠር መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ የምርጫ ጣቢያዎች ሰው አልባ ሆነዋል ተባለ

የወያኔን የይስሙላ ምርጫ ለማካሄድ የመራጮች ምዝገባ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ቢሆንም ፣ የምርጫ ጣቢያዎቹ ግን ሰው አልባ መሆናቸውን የምርጫ ምዝገባ ጣቢያዎችን ተዘዋውሮ የተመለከተው ሪፖርተራችን ዘግቧል።

ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ የሚገኙ የምርጫ ምዝገባ ጣቢያዎችን ተዘዋውሮ በመጎብኘት ለማረጋገጥ እንደቻለው በአብዛኛው ቦታዎች የተሰማሩት መዝጋቢዎች ተመዝጋቢዎችን ባለማግኘታቸው ቁጭ ብለው ቡና ሲጠጡ እንደሚውሉ ለማወቅ ተችሏል።

የተለያየ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን አስተያየት ለማወቅ በተደረገው ሙከራም በመጭው ግንቦት ወር ወያኔ ሊያካሂደው በሚዳክርበት በዚህ ምርጫ ህዝቡ ምንም ለውጥ ይመጣል ብሎ እንደማይጠብቅ ወይም ከልቡ እንደማያምን ታውቆአል። አንዳንድ ነዋሪዎች የ97ቱ ምርጫ ልጆቻችንን ከማስገደል ፣ ቤተሰቦቻችንን ከማፈናቀል እና ሁላችንም ተጠቂ የሆንበትን የኑሮ ውድነቱ ከማስከተል የዘለለ ያመጣልን ነገር የለም፣ ዘንድሮም ተመልሰን የምንታለልበት ነገር ስለማይኖር ምርጫ የሚባል ነገር ስሙንም መጥራት አንፈልግም ብለው እንደሚናገሩ ዘግቧል። አሁን በመመዝገብ ላይ ያሉት በአብዛኛው የትግራይ ተወላጅ የህወሀት አበላትና ደጋፊዎች መሆናቸውን የገለጸው ሪፖርተራችን፣ በተለያዩ ቦታዎች የሚጠየቀው የብሄር ማንነት በዘንድሮው የምርጫ መመዝገቢያ ላይ አለመቀመጡን አረጋግጧል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት የኮንዶሚኒየም ቤቶች በህወሀት አባላት መያዛቸውን አንድ በሚስጢር የተያዘ ጥናት አመለከተ

ከደህንነት አንጻር የጥናቱን ና የአጥኚውን ስም መግለጽ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሶ ሪፖርተራችን እንደዘገበው፣ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው ከተሰሩት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት በህወሀትና በአንዳንድ የኢህአዴግ አባላት የተያዙ ናቸው። አንዳንድ የህወሀት ካድሬዎች እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ እስከ አራት ቤቶችን የያዙ መሆናቸውን፣ ቤቶችን በዘመዶቻቸው፣ በልጆቻቸው ወይም በወላጆቻቸው ስም አስመዝግበው በትንሹ እስከ 4500 ብር አከራይተው ገቢ እንደሚያገኙበት በሚስጢር የተያዘው ከፍተኛ ጥናት አመልክቷል።

የኮንዶሚኒየም ቤቶች ለደሀው ህዝብ የተሰሩ ናቸው እያለ ወያኔ በምርጫ 97 ወቅት ለቅስቀሳ አውሎአቸው የነበረ ቢሆንም፣ የአዲስ አበባ ህዝብ ምርጫውን ተከትሎ በወያኔ ላይ ባሳረፈው የማያዳግም ምት የተነሳ ቤቶቹ ደሀው ህዝብ እንዳይገዛቸው ከፍተኛ የሆነ ዋጋ ቀርቦባቸው ነበር። በአሁኑ ጊዜ የአገሪቱን ሀብት ሙሉ በሙሉ በእጃቸው እያስገቡ የመጡት ጥቂት የህወሀት አባላት፣ በውድ ዋጋ የቀረቡትን ቤቶች በጉቦ፣ በብድርና በተለያዩ ዘዴዎች እየገዙ፣ በማከራየትና ወርሀዊ ገቢዎቹን እያገኙ መሆኑ ታውቁዋል።

## ለም መሬታችንን ለባዕዳን በመስጠት ባርነትን መቀበል አንሻም!!!

ሰው ባገሩ ሰው በወንዙ
ቢበላ ሳር ቢበላ መቅመቆ
ይታወቅ የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ

አባቶቻችንና እናቶቻችን ጦር አሰልፎ የመጣን ጠላት ተፋልመው ያቆዩልንን መሬት ወያኔ ለባዕዳን ቱጃሮች ሰፍሮ ሰጥቶ ከጨረሰ ወዲያ ምን አገር አለን እንላለን? የአገራችን የመሬት ይዞታ መብት አረቦች፣ ህንዶችና ቻይናዎች እጅ ውስጥ ከሆነ እኛ ምንድነን? ማነን? ለብናኝ አፈር በመሰሰት የጎብኚዎችን እግር አሳጥበው ከሸኙ አባቶቻችንና እናቶቻችን እኩል ኢትዮጵያዊያን ነን ለማለት እንችላለን? መሬታችን ተሰጥቶ ከአለቀ ወዲያ ምን አገር ይተርፈናል?

ወያኔ ለም መሬታችንን እየመረጠ "ልማታዊ ባለሃብቶች" እያለ ለሚያሞካሻቸው ለቅርብም ለሩቅም አገራት ቱጃሮች ሰጥቶ ባዶዓችንን አስቀረን። ከሁመራ እስከ ባሌ፣ ከከፋ እስከ አፋር ባዕዳን ባለመሬት፤ ኢትዮጵያዊያን ባሎች፣ ሚስቶና ልጆች የባዕዳኑ የቀን የጉልበት ሠራተኞች ሆነናል። ባዕዳን አንደኛ ደረጃ ዜጎች ሲሆኑ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ በገዛ አገራችን ዝቅተኛውን ደረጃ ይዘናል።

መለስ ዜናዊ "ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት የግል ሃብት የሚሆነው በኢህአዴግ መቃብር ላይ ነው" ብሎ ሲደነፋ ሁላችንም ሰምተናል። ሆኖም ግን ቤተሰቦቹ፣ ጓደኞቹና ካድሬዎቹ በሺህዎች ጋሻ ተመርተው ድሃው አርሶ አደር ኩርማን ሄክታር አጥቶ ልጆቹ በረሃብ እየመነመኑ ናቸው። አሁን ደግሞ ከራሱ አልፎ ለባዕዳን ለም መሬት በሺሆች ሄክታር ሰፍሮ እየሰጠ ነው። እነዚህ ቱጃሮች ለስድስት ዓመታት ግብርም ሆነ ሊዝ አይከፍሉም፤ ነፃ ነው። ከስድስት ዓመታት በኋላ ደግሞ በዓመት በሄክታር አስር ብር በማይሞላ ሂሳብ ለዘጠና ዓመታት የኪራይ ውለታ ተገብቶላቸዋል። ቱጃሮቹ ይዞታቸውን መሸጥ፣ መለወጥ፣ ማውረስ ይችላሉ። በአንፃሩ ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር ለግማሽ ሄህታር መሬት ከመቶ ብር በላይ ግብር ይከፍላል። የዘጠና ቀርቶ የአንድ ዓመት እንኳን የመሬት ይዞታ ዋስትና ስለሌለው ከዛሬ ነገ እፈናቀል ይሆን እያለ በስጋት ይኖራል። ይህን ስጋቱን የመንደር ካድሬዎችም ስለሚያውቁበት በስብሰባ፣ በመዋጮ፣ በምርጫ ድምፅ ሳይቀር ያዋክቡታል። ይህ ምን ዓይነት አገዛዝ ነው? ይህ እንደምን ያለ ክፋት ነው? ከዚህ የባሰ ክህደትስ ከቶ የት ይገኛል?

ያኔ እንደሚያወራው ሰፋፊ መሬቶችን የመስጠት ዓላማው ግብርናችንን ለማዘመን ከሆነ ኢትዮጵያዊያን ባለሃብቶች ጠፍተው ነው እሩቅ ምስራቅ እስያ ድረስ የተጓዘው? ከዛሬ አርባና አምሳ አመታት በፊት በሁመራ፣ ተንዳሆና ስምጥ ሸለቆዎች ውስጥ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች የነበሯቸው ኢትዮጵያዊያን ነበሩ። ያኔ ኖረው ዛሬ እንደምን ላይኖሩ ቻሉ? መልሱ በጣም ግልጽ ነው። ባዕዳኑ እንጂ ኢትዮጵያዊያን አልተፈለጉም። ወያኔ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ለማዋረድ ተነስቷል።

ለመሆኑ ባለሃገሩን መሬት አልባ፤ ባዕዳንን ደግሞ ባለመሬት ማድረግ ምን ያስከትላል? ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ግብዓት መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት ከግብዓትም በላይ የፓለቲካ ሥልጣን ምንጭም ነው። ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ፓለቲካ የመሬት ጥያቄ ቁልፍ የፓለቲካ ጥያቄ ሆኖ የቆየው። በጉልተኛው ሥርዓት ገበሬው የመሬት ባለሙሉ መብት ያልነበረ በመሆኑ ደካማ ነበር። ደርግ መሬትን ከጉልተኞችም ከአርሶ አደሮችም በአዋጅ ቀምቶ የመንግሥት በማድረግ መንግሥትን አሳብጦ ገበሬውን የበለጠ አዳከመው። ወያኔ ይኸንኑ መሬት ያለአዋጅ ከመንግሥት ቀምቶ የራሱ በማድረግ ራሱን አሳብጦ ገበሬውን ከቀደሞው በባሰ አዳከመው። አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ ይህንኑ መሬት ለባዕዳን በመስጠት ገበሬውን በአጠቃላይ ከመሬት ነጥሎ የቀን ሠራተኛ እያደረገው ነው። ይህ ግፍ መቆም ይኖርበታል።

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለባዕዳን መሬታችንን፣ አገራችንን፣ ነፃነታችንን ሰጥተን ከሚገኘው ጥቅም ... ባለቅኔው እንዳለው ... ሰውነታችን ታውቆ፣ ክብራችን ተጠብቆ ሳርም ይሁን መቅመቆ መብላት እንመርጣለን። ለም መሬታችንን ለባዕዳን በመስጠት ባርነትን መቀበል አንሻም!!! አገራችንን ለማዳን ቆርጠን ተነስተናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## ወደ አረብ አገር ለግርድና ከሚላኩና በጉዲፈቻ . . . ከገጽ 1 የዞረ

እያካሄደ ነው፤ በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ውድ ቅርሳ ቅርስ በምስጥር ከአገር እያስወጣ ከቸበቸበ ቦኋላ ይህ አልበቃ ብሎት ዜጎችን ለባርነትአሳልፎ በመስጠትና በጉዲፈቻ በመሸጥ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እያግበሰበሰ ነው ብለዋል። ለም የሆነውን የአገሪቱን መሬት ለአርቦችና ለአዳዲሶቹ የኤሺያ ከበርቴዎች የመሸጥ የተጧጧፈ ዘመቻም ወያኔ አስከ ወዲያኛው በስልጣን ላይ ለመቆየት ያለውን ቅዠት ዕውን ለማድረግ ሃይሉን የሚፈታተን ተቃዋሚ ከውስጥና ከውጭ ቢነሳበት ለጥቅማቸው ብለው ከጎኑ የሚሰለፉትን የውጭ ሃይላት ለማግኘት ተብሎ የተሰላ ሃላፊነት የጎደለው ጸረ አገርና ጸረ ህዝብ የሆነ እርምጃ ነው ሲሉ ተችተዋል።"

የጥናቱ ሌላው አስደንጋጭ ውጤት ለጉድፈቻ ለባዕዳን ከሚሰጡት ህጻናቱ በአብዛኛው የሚላኩት ከኦሮሚያና ከአማራ ክልሎች መሆኑ ነው። ውጭ አገር ከሚላኩት ማደጎዎች ውስጥ ከትግራይ ክልል የሚላኩ ህጻናት በብዛት አለመኖራቸው የታወቀ ሲሆን፣ ህወሀት የህጻናት ንግዱን የሚያካሂደው የሌሎች ክልል ተወላጆችን መሆኑ የህወሀትን አጀንዳ በግልጽ የሚያሳይ ነው ተብሎአል። አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኛ እንደተናገሩት ጉዳዩ ህወአትን በአለማቀፍ ደረጃ የሚያስጠይቀው በመሆኑ፣ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አጥብቀው ሊገፉበት ይገባል። ሌላ አስተያየት ሰጪ ደግሞ ህወአት መሬቱን ለቻይና፣ ለአረብና ለህንድ ባለሀብቶች ሸጠ፣ ዛሬ ሃውልት በትግራይና በአዲስ አበባ ከተማ እንዲቆምላቸው የህወአት አባላት በሆኑ የትግራይ ተወላጆች ዘመቻ የተጀመረላቸው አጼ ዮሃንስ ሳይቀር የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉበት ከ1600 ኪሎሜትር በላይ የሆነ ለም መሬታችን ለሱዳን ተሰጠ፤ የአባይ ውሀ ባለቤትነትም ለተቀናቃኟ ግብጽ ተሸጠ፤ ይህ ሁሉ አልበቃው ሲል ለውጭ ምንዛሬ ማግኛና ለህወአት ባለስልጣናት የገንዘብ ጥም ማሪኪያ የድሃ ወገኖቻችንን ልጆች ህጻናትንና ወጣቶችን መሸጥ ተጀመረ ሲሉ በሀዘን ተናግረዋል።

ህወአት ወደሥልጣን ከመምጣቱ በፊት ትግል ላይ በነበረበት ሰዓት በወቅቱ በነበረው አስከፊ ድርቅ ለረሃብ ለተጋለጡት የትግራይ ረሃብተኞች የተላከውን የዕርዳታ ዕህል አሳልፎ በመሸጥ ከፍተኛ ሃብት ያግበሰበሰ መሆኑን አብረውት የነበሩት የቀድሞ ጓዶቹ እያጋለጡት ባለበት ሁኔታ በጠመንጃ ሃይል ስልጣን ከተቆጣጠረ ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 20 ዓመታት የዘረፍውን ተግባር በአስከፊ ሁነታአ እንደቀጠለበት የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ህወአት በዚህ ዘርፍ የሚያካህደውን ወንጀል በቅርብ የሚከታተሉ ሰው አክለው ሲናገሩ " አሁን በመደረግ ላይ ያለውን ነገር ለማመን እየተቸገርን ነው። የህወሀት ሰዎች በሰው ንግድ ላይ ተሰማርተዋል። ከውጭ አገራት ተቀባይ ሰዎችን የሚያፈላልጉት፣ ፓስፖርት አሰጥተው የውጭ ጉዳዩን ሂደት ሁሉ ጨርሰው የሚልኩት እነርሱ ናቸው። በአንድ ሰው እስከ ሰላሳና አርባ ሺብ እየተቀበሉ ናቸው። ነጻና ሉአላዊ በሆነ በየትኛውም አገር በዚህ በ21ኛው ክፍለዘመን የማይፈጸም አሳዛኝ የሰው ንግድ በአገራችን እየተፈጸመ ነው።":በማለት አሰረድተዋል።

በተያያዘ ዜና በቅርቡ በውጭ አገር የተሰራ አንድ ፊልም እንደሚያሳየው ደግሞ፣ የህወሀት ሰዎች ወላጆችን አታልለው ልጆቻቸውን ወደ ውጭ አገር ከላኩ በሁዋላ፣ ወላጆች የልጆቻቸውን አድረሻ እንዳያገኙ እያደረጉዋቸው ነው ተብሎአል። በርካታ እናቶች የልጆቻውን አድራሻ ማግኘት ተስኖዋቸው እያለቀሱ በጸጸት ሲናገሩ በፊልሙ ውስጥ መመልከት የሚቻል ሲሆን፣ የህወሀት ባለስልጣናት ግን ልጆችን በመለክ ገንዘብ መሰብሰባቸውን አሁንም አላቆሙም። የግንቦት7 ንቅናቄ ወያኔ እያካሄደ ያለውን ይህንን የለየለት አሰቃቂ የባሪያ ንግድ አጥብቆ በመቃወም ህዝባችን ሆ ብሎ በመነሳት በተባበረ ትግል ወያኔን አስወግዶ የልጆቹን በባርነት መሸጥ ማስቆም እንዳለበት ጥሪውን ያቀርባል።

## በሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ይህ ፈታሽ ግብረሀይል ምንኛውንም የጠረጠረውን ግለሰብ፣ ቤት መኪና፣ የራሱን ታጣቂዎች ጭምር በማንኛውም ቦታና ጊዜ ሰአት የመፈተሽ፣ የጦር መሳሪያ ፈቃድ መጠየቅና መሳሪያው ህጋዊ ቢሆንም የመለያ ቁጥር የሚገልጽ የይለፍ ወረቀት ከሚመለከተው አካል መያዝ አለመያዙን ማረጋገጥ፣ የማሰርና የተለያዩ እርምጃዎችን በግለሰቦች ላይ በመፈጸም መረጃዎችን የማግኘት መብት ተሰጥቶአቸዋል።

ይህ ግብረሀይል ከተቋቃመበት ጊዜ አንስቶ ማንኛውም የመንግስት ታጣቂ ሚኒሻ፣ ወታደር፣ ካድሬ፣ የወያኔ ደጋፊ የግል ታጣቂ ከመኖሪያው ወደ ማንኛውም አካባቢ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከግሉ መታወቂያና የጦር መሳሪያ መያዣ ፈቃድ በተጨማሪ የመሳሪያ አይነት ቁጥርና ግለሰቡ ሰላማዊ ሰው መሆኑን የሚገልጽ ከአካባቢው የወያኔ የጸጥታና ሚኒሻ ጽ/ቤት ወይም ከቀበሌ የይለፍ ወረቀት መያዝ እንዳለበት የውስጥ መመሪያ የተላለፈ መሆኑን ታማኝ የመረጃ ምንጮች ገልጸዋል።

መመሪያውን ተከትሎ ከታህሳስ 28 ቀን 2002 ዓም ጀምሮ ከመከላከያ፣ ከፖሊስ፣ ከልዩ ሀይልና ሲቪል ከለበሱ የደህንነት ሰዎች የተውጣጣ ቡድን በሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ከመነሻው ጀምሮ በማንኛውም ቦታ ድንገተና ፍተሻ ከመጀመሩም ባላይ ወደ ጎንደር የሚገባውንና ከጎንደር ወደ ባህርዳር የሚወጣውን ማንኛውንም አይነት መኪና፣ የታጠቀ ግለሰብና እቃ ቀንና ሌሊት መፈተሽ ተጀምሮአል።

ምንጮች እንደሚገልጹት ወያኔ እንዲህአይነት እንቅስቃሴዎችን እየወሰደ ያለው አገዛዙን እየከዱ ወደ ተቃዋሚዎች ጎራ የሚቀላቀሉት ታጣቂዎችና ወታደሮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ በመሄዱ ነው።

# የሕዝብ ኑሮ: በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና በኢትዮጵያ መሬት ላይ (ክፍል 2 ከፍስሐ ዘማርያም)

በአቴቪ. የውበት ሳሎን ኩሉን፤ የጥፍር፤ የከንፈር፤ የቅንድብ፤ የጸጉር መዋቢያውን በዓይነት ያለዋወጠ ሲቀባባና በልዩ ልዩ ቋንቋ ራሱንና ራሱን ብቻ ሲያንቆለጳጵስ ውሎ ያድራል። ለነገሩ ከዚህ የተለየውን (ትክክለኛውን) አማራጭ ሊወስድ አይችልም:: ምክንያቱም ተፈጥሮውን መቀየር አይችልም። የሕዝቡን ኑሮ በተጨባጭ ለመቀየር መፍጨርጨር የሕዝብ መንግሥት መሆንን ይጠይቃልና!! ይህንን ፀጋ ከየት ሊያመጣው ይችላል? ስለዚህ ነገሩ ሁሉ ከድጡ ወደ ማጡ ሆነበት። ኢሕአዴግ እንደተመኘው በሕዝብ ግንዛቤና አመለካከት ላይ ያመጣው አንዳችም ለውጥ የለም፤ ከፍርሐት በስተቀር። ሕዝቡ እያለ ያለው "ማወቁን እናውቃለን፤ ብንናገር እናልቃለን" ነው። ያም ሆነ ይህ የኢትየጵያ ሕዝብ ሕይወቱን በቴሌቪዥን ላይ እንዲህ "እየቀጨ" ነው። ዲሽ ያላችሁ እድላችሁ!!

## ስደት እንደ አማራጭ

ይህ ሁሉ ኑሮ የቴሌቪዥን ላይ መሆኑ ቀርቶ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ወጣት የመሬት ላይ የስኬት ታሪክና ምሥክርነት ቢሆን ኖሮ ሁላችንም ምንኛ ደስ ባለንና በኮራንም ነበር?! ቁጭትና ጨኸታችንስ ሌላ ለምን ሆነና? ነገር ግን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ድምፅ አልባ የኢትዮጵያ ወጣቶች የኢሕአዴግ አባል ወይም ደጋፊ ባለመሆናቸው ብቻ ይህን ለጥቂቶች በአድል- የተሰጠ ዕ ድል እንደተነፈጉ ናቸው:: እነዚህ ወጣቶች ይህን አይን ያወጣ የመሬት ላይ አድልኦና በሸፍጥ የተሞላ የኢቴቪ. ፕሮፓጋንዳ በንጽጽር ሲያዩ ናእውነት ይህ ሐገር የማን ነው? ን በማለት ልባቸው ይሸፍታል።

ወጣቶቻችን፤ የአሜሪካውን ዲቪ. ተዉትና ወደ ደቡብ አፍሪካ፤ ምሥራቅና ሰሜን አፍሪካ፤ ወደመካከለኛው ምሥራቅና የባህረሰላጤው አገሮች በገፍ የሚሰደዱበትና እዚያም ፍዳቸውን እያዩ የሚኖሩበት አንዱ ዋና ምክንያት ይህ ምሬት አይደል? የሩቁን ጊዜ ትተን፤ በቅርቡ በሱዳን፤ በሊቢያና በአረብ ኤ ሜሬቶች በስደተኛ ወገኖቻችን ላይ በየሐገሮቹ ፖሊስና በቀጣሪ-ቻቸው የተ ፈጸመባቸውን ግፍ አይተናል ሰምተናል። መከራው ማብቂያም የለው። የኢኮኖሚው ስደት ሦስተኛው የመከራ ምዕራፍ መሆኑ ነው። ከስደት የተ ጠበቀው እፎይታ ቀርቶ ሌላ ሲያል ሲገጥም የት ይደረሳል? የሐገር ቤት አስከፊው ድህነትና የኑሮ ውድነት የመጀመሪያው መከራ ነው። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እብሪተኛ ቅጥፈት ደግሞ ሌላው ህመም!

## ማገጣጠሚያ

በክፍል አንድ እንደተገለጸው፤ የዚህ ጽሁፍ ዋና ጉዳይ የአብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የመሬት ላይ ናየሲያልና ኑሮና የቴሌቪዥን ላይ ናየገነትን ኑሮ በንጽጽር ማየት ነው። ንጽጽሩ የፕሮፓጋንዳውን ዓይን ማውጣትና ጎን ለጎንም የሕዝቡን የኑሮ ችግር ጥልቀት እንዲሁም አንገብጋቢነቱን በይበልጥ ለመገንዘብ ይጠቅም ይሆናል። ኑሮአቸው በእጅጉ ተሻሻለ የተባሉ ጥቂትሰዎች እንዲሁም የቁጥር መስፈሪያ የማያውቃቸውና በመሬት ላይ የማናያቸው ሌሎች መናፍስትም በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ነጋ ጠባ ይቀርቡልናል። በክፍል አንድ፤ የፕሮፓጋንዳው ባህርይ፤ ተልእኮ፤ ላማ፤ይዘትና አቀራረብ ተዳሷል። በዚህ በክፍል ሁለት ደግሞ በኢቴቪ. ከሚቀርብልን የምናባዊ ፍጡራን "የድሎትና የምቾት ኑሮን" በተቃራኒው ያለውን ዕውነ፤ እናያለን። ስለራሳችን ስለተራ ሰዎች ማለትም ሥጋና ነፍስ ስላለን ግለሰቦች፤ ስለቤተሰቦቻችን፤ ስለጎረቤቶቻችን፤ ስለሥራ ባልደረቦቻችንና ስለ ወገኖቻችን በመሬት ላይ የሚታየውን በመከራ የተሞላ የዕለት ኑሮ፤ ቦታ፤ ጊዜና ሁኔታዎችን እያጣቀስን እኛው ራሳችን እንናገራለን - እንነጋገራለን። ይህንንም ሳናወሳስበው በራሳችን በተራሰዎች የዕለት በለት ቋንቋ ለመግለጽ እንሞክራለን።

በዚህ ክፍል የሚቀርበው ጽሁፍ የመደበኛ (የመስክ፤ የቤተመጻህፍት) ምርምር ውጤት አይደለም። በዋነኛነት (ከነጉድለቱም ቢሆን) አቅም የፈቀደውን ያህል ረዘም ላለ ጊዜ የተደረገ የምር አስተውሎትና ማሰላሰል ውጤት ነው። ጥቂት ከማይባሉ ባለጉዳዮች ጋር በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የምር ውይይቶች ለጽሁፉ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። አንዳንዱን መደምደሚያዬን ደፋር ሆኖ የሚያገኘው አንባቢ በራሱ መረጃና ማስ ረጃ ያስተ ክለው። እኔ ግን የማየው እንደዛው ነውና ከመግለጽ ሌላ አማራጭ አላገኘሁም። የንዴት ስሜት ያዘሉ አረቦችም ከበዙ ከፊሎቹን ልደብቃቸው ስላልቻልኩ ነው፤ ከፊሎቹ ግን ከእርማት ያመለጡ መሆን አለባቸው። ለሁሉም ይቅር፤!

የኢኮኖሚ ዕድገትና ውድቀት ትንታኔውን፤ ቁጥሩንና ቴክኒካዊ ቋንቋውን ባለሙያዎቹ ይሉታል። በኢኮኖሚ መጻህፍት፤ የጥናት ወረቀቶችና የፖሊሲ ሠነዶች ላይ የሚቀርቡት ዓይነት ምሁራዊ ክርክሮችና ዝርዝሮችም እዚህ አይገኙም። እዚህ የሚቀርቡት የአስከፊው ኑሮአችን ልዩ ልዩ ማሣያዎች ናቸው። እዚህ ያልተገለጹ የአስከፊው ኑሮአችን ማሣያዎች እንደሚበዙና እንደሚከፉም እርግጥ ነው። ሌሎች ዜጎችና ሕዝባዊ ምሁራን በሚያደርጉት የተሻለ አስተዋጽዖ ይበልጥ ሥጋና ነፍስ ያላቸው፤ የተለያዩና ሁሉን አቀፍ የሆኑ የኑሮአችን ማሳያዎችን እናገኛለን። እነዚህን ከነመንስኤና የመፍትሔ ሐሳባቸው ለውይይት በማቅረብና በማዳበርና ለህዝባዊ ትግሉ ግብዓት ማድ ረግ ነው ትልቁ ነገር። የንጽጽሩን የተሟላ ሥዕልና መልእክት ማየት እንዲቻ ል፤ የዚህ ጽሁፍ ክፍል አንድ በቅድሚያ ወይም ከዚህ በኋላም ቢነበብ ጥሩ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ በመሬት ላይ የሚታየው የታችኛውና የመካከለኛው መደብ የከተማ ሕብረተሰብ የዕለት ኑሮ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተለውን ይSስላል።

## የሕዝብ ኑሮ በኢትዮጵያ መሬት ላይ - በእኛው ዓይን!

### በቆሎ፤ ድንችና ጎመን ላይ መድረስ ከባድ ነው

አብዛኛው ሕዝብ የጤፍ እንጀራ፤ የስንዴ ዳቦ፤ የገበስ ቆሎ፤ የዘይትና የበርበሬ ሹሮ ወጥ ለዓመት በዓል እንኳን ብርቅ ሆኖበታል። ለወትሮ ቀለል ባለ ዋጋ ይገኝ የነበሩ እንደ በቆሎ፤ ድንችና ጎመን የመሰሉ ምግቦችም የአዘቦት ምግብነታቸው በጣም እየቀነሰ ነው። አብዛኛው ሕዝብ በቀን ሦስት ጊዜ የነፍስ ማቆያ እነሱን እንኳን መቅመስ የማይችልበት ደረጃ ደርሷል። በዚህ ምትክ የቤተሰብ አባላት (ወላጆችን ተዉና ልጆቻቸው) ምሣና እራትን በፈረቃ መቃመስ ግድ ሆኖባቸዋል። በርካታ ተማሪዎች ምግብ ሳይቀምሱ ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸው የተለመደ ነው። ይህንን ወደታች በዝርዝር እንመለስበታለን።

መደበኛ ምግብና ቡና ቤቶችን ተሰናብቶ መደበኛ ያልሆኑ የሜዳ ላይ ምግብና ሻይ መሸጫዎች ደምበኛ የሆነው ተጠቃሚ ቁጥሩ በጣም ጨምሮአል። መደበኛ ያልሆነ የልባሽ ጨርቆችና የቤት ዕቃዎች ንግድም በየጎዳናውና በየጥጋጥጉ ተስፋፍቷል። የነዚህ አገልግሎቶች አብዛኛው ተጠቃሚም የወትሮው ሣይሆን አዲስ ደንበኛ ነው። የጎዳና ምፋብ ቤቶች አዲሶቹ ደምበኞች ማናቸው? ቀደም ብለው ከነበሩበት የተሻለ የኑሮ ደረጃ (ከዝቅተኛው የመካከለኛ መደብ) በኑሮ ውድነቱ ተገፍትረው ወደ ዝቅተኛው መደብ የወረዱና ወደዚህ የመጡ ናቸው:: ዕውነቱ ከኢቴቪ. አደንቋሪና አናዳጅ ፕሮፓጋንዳ ፍጹም ተቃራኒ ነው። ናእድሜ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሥመራችንና ለፈጣኑ የኢኮኖሚ ዕድገታችን፤ ብዙ ሕዝብ ከዝቅተኛ መደብ ወደ መካከለኛ መደብ አድጓልን ይለናልኢቴቬ - ያለአንዳች ሐፍረት:: በነገራችን ላይ አዲሶቹም ደንበኞች ቢሆኑ በጎዳና ምግብ ማቅረቢያዎች መስተናገድ የቻሉት ሥፍራው በሽግሽግ ተለቆላቸው ነው። የጎዳና ተዳዳሪዎች፤የቀን የጉልበት ሥራ ሠራተኞች፤ ሊስትሮዎች፤ ሲጃራ፤ ሎተሪ፤ ቆሎና ሶፍት አዟሪዎች ወዘተ፤ እነዚህ ነበሩ የቀድሞ የጎዳና ምግብ ቤቶች የታወቁ ደንበኞች። ዛሬ በዚያ ሥፍራ የሉም። በጎዳና ላይ፤ በአውቶቡስ መናኸሪያዎች ጥግ፤ በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ፤ በዛፎች ጥላና በቆንጥሮች ሥር ይቀርቡ የነበሩት የተቀቀለ ድንችና በቆሎ፤ ቂጣ በጎመን፤ቂጣ በአቦካቶ ወይም በሙዝ፤ ዳቦና ፓስቲ በሻይ፤ ሸንኮራ፤ የባቄላ አሹቅና ቆሎ ወዘተ ነበሩ። በወትሮ ሥፍራቸው ለወትሮ ደንበኞቻቸው እየቀረቡ አይደለም:: ዛሬ ግን በነርሱ ምትክ በላስቲክ ጥላ ሥር በአግዳሚ መቀመጫዎች ላይ የሚስተናገዱት አዲሶቹ ግፉአን ደንበኞች፤ በየቢሮው የሚሠሩ የበታች ሠራተኞችና አነስተኛ ገቢ ያላቸው ወንደላጤዎች ናቸው። እነዚያ የቀድሞዎቹ ግፉአን ደንበኞች ከዚህም ተገፍትረውና ተወርውረው ምን ዓይነት የኑሮ አዘቅት ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ ገምቱ።

በአዲስ አበባ መርካቶ ጥጋጥጎች ከምግብ ቤቶች በትርፍራፊነት የተሰበሰበ ምግብ በጉርሻ ደረጃ መሸጥ ከተጀመረ ሰነበተ። ግማሽ ወይም ስስ እንጀራ አይደለም እየተባለ ያለው። በመርካቶ አንድ - ሁለት ጉርሻ እንጀራ ይሸጣል ነው እያልን ያለነው። ከግፉአንም ግፉአን የሆኑ ዜጎቻችን፤ አንድአንድ የእንጀራ ጉርሻ (መካከለኛ ወይም ትልልቅ) በሳንቲም ቤት ገንዘብ እየከፈሉ በሰልፍ ተራ ገብተ ው እየጎረሱ ያልፋሉ፤ እናም በዚሁ ይውላሉ / ያድራሉ። እናም በረሀብ የተጎዳ አንጀታቸውን አስረው በመስጊድና ቤተክርስቲያኖች አጥር ሥር፤ በመቃብር ሥፍራዎች፤ በከተማ ፍሳሽ ውቼ መውረጃ ቱቦዎች ውስጥ፤ የተሻሉት ደግሞ በአውቶቡስ ፌርማታና በረንዳ፤ እንዲሁም በጋራ የኪራይ ማደሪያዎች ውስጥ ፈስሰው ሌሊቱን ያሳልፋሉ። የላስቲክና የካርቱን ናቤቶችምን በዚህ ዝርዝር ውስጥ አሉ። ሥራ ወይም ገበያ ስለሌለ የግዢ ጉርሻም እንኳን ሳይቀምሱ ጦማቸውን ለመዋልና ለማደር የሚገደዱትም መሰል ዜጎች ሥፍር ቁጥር የላቸውም።

ከኑሮው ትግል ገና ጨርሰው ተገፍትረው ያልወደቁ በመጠኑ ሻል ያሉት ደግሞ እንዲህ ያደርጋሉ። እንደወትሮው ለዓመት በዓል በግና ወይም የበሬ ቅርጫ ሥጋ በቤተሰብ ደረጃ መግዛት ቅንጦት ሆኖባቸዋል:: የደሞዝ ሰሞንም ኪሎ ሥጋ በግል መግዛት እንዲሁ። ስለዚህ በጎረቤት ደረጃ ለሁለትና ለሦስት አንድ ኪሎ ሥጋ በቅርጫ ናማስገባትንን እየተለማመዱ ናቸው። ሰው አየኝ አላየኝ በማለት እየተሸማቀቁም ቢሆን ሩብ ኪሎ ወይም ቅንጥብጣቢና እንደነገሩ የሆነ ሥጋ መግዛት መቻልም ናመታደልና ሆኖአል:: ወተትና ዕንቁላልማ ሰፊው ሕዝብ ጋ በየት በኩል ደርሰው። አቅርቦትና ፍጆታቸው በሥዕል ደረጃ ሆኖአል። በጤና ጣቢያ የጤና ማስተማሪያ ሥዕሎች (ቻርትና ፖስተሮች) እና በንግድ ማስታወቂያዎች ላይ ይገኛሉ። ያሳዝናል!!

### በግልጽ የማይታዩ አሳዛኝ የኑሮ ገጽታዎች

ሌሎችም በቀላሉ ሊታዩ የማይቻሉ አሳዛኝ የኑሮ ገጽታዎች አሉ። በወፍጮ ቤት ጤፍ ሲበጠር በንፋስ የሚንገዋለለው ብጣሪና ትርፍራፊው ለብቻ ው ይሰበሰባል። እናም ወደ ሌላ አካባቢ ተወስዶ ለድሃው ከተሜ እንዳቅሙ ይሸጥለትና እርሱም ናጤፍን በልቶ ያድራል:: ትንሽ ንጹህ ጤፍ ገዝቶ ያንን ለማበራከት በዋጋ ረከስ የሚሉትን ማሽላና በቆሎ ቀላቅሎ የሚያስፈጨው የሕብረተሰብ ክፍልም በጣም ብዙ ነው:: የድህነቱ መክፋት ከወፍጮ ቤቶች ጋር የተያያዘ ስርቆሽና የሚስጥር ገበያዎችንም መፍጠር ጀምሯል። እንደነገሩ የሞላላቸው አስፈጪዎች የሚያመጡት ድቄስ በርበሬ ከተፈጨ በኋላ የባለቤቶቹ መዘናጋት ታይቶ ከፊሉ በዘዴ እዚያው በወፍጮው ቋት ውስጥ ተቀንሦ ይቀራል:: በኋላ ላይ በደንበኝነት የሚታወቁ የጉልት ነጋዴዎች በአነስተኛ ዋጋ በሚስጥር ይረከቡታል:: እናም ኑሮ እያንገዳገዳቸው ያሉ ወገኖች በማይታመን ቅናሽ ዋጋ ከነዚህ ጉልቶች ገዝተው ቤታቸው ያስገቡታል።

በግንባ፤ ፕሮጀክቶች ውስጥ በጉልበት ሥራ ላይ የተሰማሩ የቀን ሠራተ ኞች፤ በጣም ትናንሽ የሆኑ የንግድ ሥራዎች የሚሠሩ፤ በተመላላሽነት በሦስት አራት ሰው ቤት ተቀጥረው የሚሰሩና በሌሎች መሰል ሥራዎች ላይ የተሠማሩ በአብዛኛው ሴት እህቶቻችንን እንውሰድ። ኑሮአችሁ እንዴት ነው? ምኑን ከምኑና እንዴትስ፤ ብቃቂታላችሁ? በሉና የነሱ ሰው ሆናችሁ፤ በሐቀኛ ተቆርቋሪነት መንፈስ ቀርባችሁ ጠይቋቸው። ለምሳሌ ማገዶ ከየት በስንት ያገኛሉ? አንድ ጆንያ ከሰል እንደሆነ ዋጋው ከ80 እስከ 110 ብር ስለሆነ ለነዚህ ወገኖቻችን (በችርቻሮ ደረጃም ቢሆን) የማይታሰብ ነው:: ነገር ግን እነርሱም ናከሰልን ገዝተው ምግባቸውን (በቆሎና ጎመናቸውን) እንደሚያበስሉ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው እያመነቱ ይነግሯች ኋል። የነርሱ ናከሰልን ምንጩ የት ነው? በአብዛኛው ከምግብና ሻይ ቤቶች ምድጃ ውስጥ ታፍሶ የሚወጣው የአመድ ጥራጊና የልዩ ልዩ ደረቅ ሕሻሻዎች ጥራጊ ነው። ይህ በቆሻሻ አንሺዎች ተሰብስቦ በከተሞች ዳርቻ ወደሚገኙ የቆሻሻ መጣያዎች ይራገፋል። ከነዚህ ሥፍራዎች ላይ ለድሆች ማገዶ ሊሆን የሚችለውን ለይተውና በብዛት ሰብስበው በጉልት ገበያ ላይ በርካሽ ዋጋ ለሽያጭ የሚያቀርቡ ሌሎች ወገኖች አሉ። በዚህ መንገድ የተገኘውንና ከጉልት የገዙትን ናከሰልና፤ ገና ስናያይዘው ትንሽ ሽታው ያስቸግረናል እንጂ ምንም አይልም ይሏችኋል።

**(ክፍል 3 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል)**

## የወያኔ ሹመኞች ሆን ብለው የንግድ ቤቶቻቸው እንዲቃጠሉ እንዳደረጉባቸው የኮልፌ አካባቢ ነዋሪዎች ገለጹ

በኮልፌ ነዋሪዎች ሙሉ መዋጮ የተገነባው እፎይታ እየተባለ የሚጠራው ህንጻ በእሳት መጋየቱን ተከትሎ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች የወያኔ ካድሬዎች እንዳቃጠሉባቸው በመግለጽ ላይ ናቸው። ሪፖርተራችን በንግድ ማእከሉ የሚገለገሉ አንዳንድ ነጋዴዎችን አነጋገርሮ እንደዘገበው የወያኔ ባለስልጣናት በኮልፌ አካባቢ ባለው የንግድ እንቅስቃሴ ተደጋጋሚ የሆነ ቅሬታ ሲያቀርቡና ህንጻው የሚፈርስበትንም ዘዴ ሲያሰላስሉ ነበር።

በጥምቀት በአል እለት በተነሳው ቃጠሎ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ንብረት እንደወደመ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ የአካካቢው ነዋሪዎች እንደሚናገሩት ማንም በአካካቢው በሌለበት ሁኔታ እሳት መነሳቱ፣ እሳቱም ከተነሳ በሁዋላ የእሳት አደጋ መኪናው የደረሰው ከላይ የሚገኙትን የተለያዩ ሱቆችን ካወደመ በሁዋላ ፣ ምድር ላይ የሚገኝ አንድን ባንክ ለማዳን መሆኑ የወያኔ እጅ እንዳለበት አያጠራጥርም ብለዋል። የኮልፌ አካባቢ ነዋሪዎች እንደሚሉት ወያኔ አካባቢውን በታማኝ ሰዎቹ ለማስያዝ ከብዙ አመታት በፊት ጀምሮ ሙከራ ቢአደርግም፣ የአካካቢው ተወላጆች ሁሌም በአንድነት በመቆማቸው የወያኔን እቅድ ሲያከሽፉ ቆይተዋል። አሁንም ይላሉ የኮልፌ ነዋሪዎች፣ ከምግባችን እየቀነስን ህንጻውን መልሰን እንሰራለን እንጅ ለወያኔ ሰዎች አናስረክብም ሲሉ ተናግረዋል። የኮልፌ አካባቢ ተደጋጋሚ የእሳት ቃጠሎ እንደሚነሳበት ቢታወቅም፣ ያካካቢው ህዝብ ግን ሁሌም ወያኔ ነው የሚያስነሳው የሚል መልስ እንደሚሰጥና ያካባቢው ህዝብና ወያኔ እሳትና ጭድ መሆናቸው ይታወቃል። በግንቦቱ ምርጫ ወቅት በአብዛኛው ታፍሰው የታሰሩት ወጣቶች የኮልፌ አካባቢ ልጆች እንደነበሩ ይታወቃል።

## በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ እየተበላሸ መሄዱን ሂውማን ራይትስ ወች የተባለው ታዋቂ አለማቀፍ ተቋም አስታወቀ

ተቋሙ የምእራባዊያን መንግስታት የሰብአዊ መብቶችን ከሚጥስ የወያኔ አገዛዝ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመስረታቸውን በእጅጉ ኮንኗል። የፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደርም በኢትዮጵያ እና በሌሎች አገሮች በሚታዩ አምባገነን መንግስታት ላይ የቡሽ አስተዳደር ሲወስድ ከነበረው እርምጃ የተለየ እርምጃ እየወሰደ ባለመሆኑም ወቀሳ አቅርቧል።
አለማቀፉ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ድርጅት ይፋ ባደረገው ሪፖርት የወያኔ አገዛዝ የፈጸማቸውን በርካታ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አጋልጧል፣ አንዳንዶችም በጦር ወንጀለኝነትና በሰው ልጆች ላይ በተፈጸመ ወንጀል በአለማቀፍ ፍርድ ቤት የሚያስጠይቁ መሆናቸውን ገልጿል።

ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ ከ200 መቶ የማያንሱ ሰዎች በወያኔ ፖሊስ መገደላቸውን፣ የተቃዋሚ መሪዎችን በማዋከብ በአገሪቱ ውስጥ የተቃውሞ ፖለቲካ እንዳይኖር መደረጉን፣ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የሆነችው ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ወደ እስርቤት ተመልሳ መላኩዋን እንዲሁም ፍጹም የሆነ የጭቆና አገዛዝን ለማስፋፋት በአለም ላይ ታይቶ የማይታወቅ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚያፍን እና በጸረ ሽብር ትግል ስም የፖለቲካ ተቃውሞዎችን ለማፈን ህግ መውጣቱን ተቋሙ ዘርዝሯል ። አዲሱ የጸረ ሽብር ህግ የፖለቲካ ተቃውሞ የሚያነሱትን ሁሉ በአሸባሪነት የሚፈርጅ እጅግ አደገኛ ህግ ነው ብሎአል።

ምርጫ 2002 እየተቃረበ ሲመጣ፣ ጠባብ የሆነውን የፖለቲካ ሜዳ ይበልጥ የሚያጠብ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ነው የሚለው ተቋሙ፣ መንግስትን የሚተቹ ዜጎች ተደጋጋሚ እሰርና ማወከብ እንዲሁም የጸረ ሰላም ሀይሎች አባላት ናችሁ እየተባሉ ስቃይ ይደርስባቸዋል ሲልም ገልጿል። ወያኔዎች ታዋቂ የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆኑትን አቶ አበበ ወርቄን በሀሰተኛ ክስ ከሰው ከአገር እንዲወጡ ማድረጋቸውን፣ ለእርዳታ የሚመጣውን እህል ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ ወይም ተቃዋሚዎችን የሚደግፉ ሀይሎችን መቅጫ መጠቀማቸውን ሪፖርቱ አመልክቷል።

በርካታ የኦሮሞ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት በእስር ላይ መገኘታቸውንና በፖሊስና በመከላከያ እስር ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ዜጎች በእስርቤት ውስጥ የተለያዩ አሰቃቂ ድርጊቶች እንደሚፈጸሙባቸው አጋልጧል።

በወታደሮች የተፈጸሙ አሰቃቂ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችንም በመዘርዝር አንዳንዶች በጦር ወንጀለኝነትና በሰው ልጆች ላይ በተፈጸሙ ወንጀሎች የሚያስጠይቁ መሆናቸውን ገልጾ፣ እነዚህን አሰቃቂ ወንጀሎች የፈጸሙት ወታደራዊ አዘገኖች ወይም የፖለቲካ መሪዎች ለፍርድ ለማቅረብ ጥረት አለመደረጉንም ተችቶአል። ወያኔ በጋምቤላ በተፈጸመው ግድያ የተወሰኑ ወታደራዊ አዘገኖችን ተጠያቂ ለማድረግ የይስሙላ ሙከራ ያደረገ ቢሆንም፣ በሶማሊያ ወረራ ወቅትና በኦጋዴን አካባቢዎች ለተፈጸሙት ወንጀሎች ማንም ተጠያቂ አልሆነም ብሎአል።

የወያኔ አገዛዝ በአለም ላይ በምጽዋት ከሚኖሩ መንግስታ መካከል አንዱ በመሆን በአመት ከ2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ በእርዳታ መልክ እንደሚያገኝ ሪፖርቱ ጠቅሶ፣ በርካታ ለጋሽ አገሮች የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እያወቁ እንኳን የሚሰጡት እርዳታ እንዳይቋረጥ በመፍራት በወያኔ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ትችቶችን ለማቅረብ አይደፍሩም በማለት የውጭ መንግስታቱን አቋም ነቅፏል። መሰረታዊ የሆነ የፖሊሲ ለውጥ መምጣት ያለበት ከፍተኛ እርዳታ ከምትሰጠው አሜሪካ መሆን አለበት የሚለው ሂውማን ራይትስ ወች፣ የፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደር ግን ከቡሽ አስተዳደር የተለየ እርምጃ እየወሰደ እንዳልሆነ በመጥቀስ ሪፖርቱን አጠቃልሎአል።

## የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በተያያዘ ዜናም የኑሮ ውድነቱ በየጊዜው እየከፋ መሄዱን ነወሪዎች በመናገር ላይ ናቸው። “በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የኑሮ ውድነት በቃላት ለመግለጽ የማይቻል ነው። ሁሉም ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ነው። የት እንደምንደርስ አናውቅም” ሲሉ አንድ እናት መናገራቸውን ሪፖርተራችን ዘግቧል። የጥር ወር በተለምዶ የእህል ዋጋ የሚረክስበት ወቅት ቢሆንም፣ ባሁኑ ጊዜ የጥር ወር የእህል ዋጋ የሚወደድበት ወር ሆኗል ሲሉ እኝህ እናት መናገራቸውን ገልጿል። በመንገስት ስራ ላይ የሚተዳደሩት አቶ አያሌው ማሞ የተባሉት የአዲስ አበባ ክልል ነዋሪ በበኩላቸው ሲናገሩ ፣ ሁሉንም ነገር ወደ ላይ እየወጣ ሲሄድ የእኔ ደሞዝ ግን ወደ ታች ነው የሚሄደው እናም ልጄቼን ማስተዳደር የማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ፣ ምንገስት ልጆቼን ካልተረከበ ወይም ወደ ውጭ የሚልክ ድርጅት መጥቶ ካለወሰዳቸው አሁን ባለው አቅሜ ማስተዳደር አልችልም ይላሉ።

አቶ አያሌው ከበርካታ የስራ አገልግሎት በሁዋለ የሚከፈላቸው ደሞዝ 835ብር መሆኑን ተናግረው፣ ይህ ገንዘብ ከአምሳ ኪሎ ጤፍ የበለጠ ነገር እንደማይገዛ ተናግረዋል። ድሮ ይላሉ አቶ አያሌው በ250 መቶ ብር ቤተሰቤን ቀጥ አድርጌ ይዢ ነበር፣ ዛሬ በስምንት መቶ ብር አንድ እንጀራ በልቶ ለማደር እየቸገረን ነው። ምን አይነት ጊዜ እንደመጣብን አላውቅም ሲሉ ገልጸዋል።

በሌላ ዜና ደግሞ የወያኔ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ ገቢ አሁንም ጫት መሆኑ ተገለጸ። በአዜብ መስፍን የበላይ ጠባቂነት የሚካሄደው የጫት ንግድ ዘንድሮም የውጭ ገቢ በማስገኘት በኩል ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል። አገሪቱ በስድስት ወር ውስጥ ካገኘቸው 700 ዶላር ውስጥ ከ100 ሚሊዮን ዶላር ያላነሰው ገቢ የተገኘው ከጫት ንግድ ሲሆን፣ ብዙ የተባለለትና በዶ/ር ኢሌኒ ገብረመድህን የተቋቋመው የቡና ዝውውር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ውጤቱ አሽቆልቁሎ መታየቱን ምንጮቻችን ገልጸዋል።

## በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው የጸጥታ ሁኔታ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ ይህን ያክል ሰራዊት በአሁኑ ጊዜ ለማሰማራትየፈለገው፣ በአካባቢው እያየለ የመጣው የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ወያኔን እንቅልፍ እየነሳው በመምጣቱ፣ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን የሚሰጥበት የመጨረሻው ምእራፍ ላይ መድረሱ በርክክቡ ወቅት የሚነሳውን የህዝብ ተቃውሞ ለማፈን፣ እንዲሁም ከዚህ ቀደም የጎንደር መሬት የሆነውን ወልቃይት ጠገዴንና የወሎ መሬት የሆነውን ኮረምን፣ አላማጣንና የቆቦን ለም መሬቶች ወስዶ የትግራይን ሪፑብሊክ ለመመስረት ያቀደውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ መሬት ለመውሰድ በማሰቡ የሚነሳበትን ተቃውሞ ለማፈን ነው።

አሁን ወያኔ ከአማራው ክልል ወስዶ ወደ ትግራይ ክልል ለመቀላቀል ያሰበው መሬት የጠገዴ ወረዳ አካል የሆነውን ከአብራጂራ ከተማ ምስራቃዊ አቅጣጫ አንገረብ ወንዝን ተሻግሮ በጣም ለም የሆነውን የማትአርጊን፣ ወንደርጌን፣ ኪሻንና ምርዘነብ የሚባሉ ቀበሌዎችን መሬት ጨምሮ እስከ ዘመነ መሪቅ ምስራቃዊ ጫፍ ድረስ ያለውን ሰፊና ለም መሬት መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዋል። ከስፍራው በደረሰን መረጃ መሰረት በአሁኑ ጊዜ በእነዚህ አካባቢዎች ያሉት የመንግስትና የግል ታጣቂዎች በትግራይ ክልል እዝ እንዲታዘዙና ማንኛውም የመንግስት ንብረት በትግራይ ክልል እንዲተዳደር እየተደረገ ሲሆን የአካካቢው ህዝብም ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ በማሰማት ላይ ነው።

ወያኔ ከአማራ ክልል መሬት በመውሰድ ትግራይን የማስፋቱ እንቅስቃሴ በሌሎች አቅጣጫዎችም እየተከናወኑ መሆናቸውን ምንጮቻችን ይገልጻሉ። በሰሜን ምእራብ አርማጭሆ አካባቢ የሚገኘውን አቢጢርን፣ ገላሉቫን፣ ኮረደምንና አብድራፊን ጨምሮ በጣም ለም የሆነውን መሬት ወደ ትግራይ ለመውሰድ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን መረጃው አመልክቷል።

## የወያኔ የምርጫ ጣቢያዎች . . . ከገጽ 1 የዞረ

ሪፖርተራችን እንደዘገበው በየትኛውም የመንግስት መስሪያቤት ሰዎች የብሄር ማንነታቸውን ሳይጠየቁ ስራ መስራት አይችሉም፣ ይሁን እንጅ በዘንድሮው ምርጫ በአዲስ አበባ የብሄር ማንነት የሚለው ጥያቄ ቀርቷል፣ ይህም የሆነበት ምክንያት ወያኔ አብዛኛው ተመዝጋቢ ከየትኛው ክልል እንደመጣ እንዳይታወቅበት በመፍራት ነው ብሎአል። የተወሰኑ ናሙናዎችን ወስዶ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በአንድ ሰንጠረዥ ውስጥ ከተመዘገቡት ሰዎች መካከል አብዛኞቹ ስማቸው ከአንድ ክልል የመጡ መሆናቸውን ይጠቁማል ብሎአል።

በተያያዘ ዜናም የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎችን የማሰሩና የማዋከቡ ድርጊት መቀጠሉን ሪፖርተራችን ዘግቧል። በርካታ የመድረክ አባላት በስርቆት፣ በመሳሪያ ቅሚያና በሌሎችም የተቀነባበሩ የሀሰት ወንጀሎች እየተከሰሱ ፍርድ ቤት በመቅረብ በምርጫው እንዳይሳተፉ እየተደረጉ እንደሚገኙ ዘግቧል። ፍርድቤቶች ፣ፖሊስና የደህንነት ሰራተኞች በጋራ በመሆን፣ የተቃዋሚ እጩዎችን ቤቶች ፈትሸው መሳሪያ እንዳገኙ በማስመሰል ግለሰቦችን ወደ ፍርድቤት ወስደው እንዲታሰሩ በማድረግ ላይ ናቸው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661 ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን